የመላዉ ኢትዮጲያ አንድነት ድርጅት
All Ethiopian Unity Party (AEUP)

October 9, 2008

## ለቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማኅበራት በአሜሪካ

ጉዳዩ፤ ስለ October 17, 2008 ስብሰባ ጥሪ ማብራሪያ

እንደሚታወሰዉ በSeptember 24, 2008 በአሜሪካ የሚገኙት ድጋፍ አካሎቻችን በኩል የተከሰቱትን ችግሮች በመፍታት ትግሉ ዉጤቶችን እንዲያስመዘግብ ለማድረግና ከድጋፍ ማኅበራት የሚጠበቀዉን አስተዋጽኦ ለመወያየት እንዲያስችል በOctober 17, 2008 በዋሽንግተን ዲሲ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ጥሪ አቅርቤአለሁ።

የዚሁም October 17, 2008 ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ጥሪ በአጠቃላይ በአሜሪካ የሚገኙትን ድጋፍ አካላትን እንዲያሳትፍ የታቀደ ለመሆኑና እያንዳንዱም ድጋፍ አካል በትክክለኛዉ መስመርና መንገድ የወከለዉን ተጠሪ ለስብሰባዉ እንዲያቀርብ በቅድሚያ ለማሳወቅ እወዳለሁ።

የስብሰባዉም ተግባራት፤

1ኛ - ድጋፍ አካሎቻችን የፈፀሟቸዉን ተግባራትና ከገንዘብ አሰባሰብ ጀምሮ በወቅቱ በሥራ ላይ የገጠማቸዉን ችግሮች በሪፖርት መልክ እንዲያቀርቡ፤

2ኛ - የአሜሪካ ድጋፍ ሰጪ አካልን የሚያጠናክሩ ሐሳቦችን ይዘዉ እንዲገኙ።

3ኛ - የቅንጅት አማካሪ ቦርድም ለዚሁ ስብሰባ ዝግጅት አስፈላጊዉን ትብብር እንዲያደርግና በስብሰባዉም ወቅት ድጋፍ ሰጪ አካሉን የሚያጎለብቱ ምክሮችን እንዲያበረክት።

ድል ለኢትዮጲያ ሕዝብ ፤
የዴሞክራሲ ትግላችን ይቀጥላል !

አባይነህ ብርሃኑ
የመኢአድ ም/ሊቀመንበር